

# የጳውሎስ ጉብኝት በቆሮንቶስ

- ጳውሎስ ከአቴንስ ተንስቶ ወደ ቆሮንቶስ ከተማ ተጓዘ። ሲላስና ጢሞቲዎስም በመጨረሻ ከጳውሎስ ጋር በቆሮንቶስ ከተማ ተገናኙ። ጳውሎስ በዚያ ለሚገኙ አይሁዳውያን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰበከላቸው። ሆኖም ለማመን ፈቃደኞች አልነበሩም። እንደውም በክፋት ተነሱበት። ከጥቂት ጊዜ በኋላም በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን ዝግጁ መሆናቸውን ወይንም አለመሆናቸውን ጠየቃቸው። ምክንያቱም  ምላሻቸውን ከሰማ በኋላም አይሁዳውያን ላልሆኑት መስበክ እንዲችል! እንዳለውም በቆሮንቶስ ከተማ ለሚገኙና አይሁዳውያን ላልሆኑት ኢየሱስ ክርስቶስን ሰበከላቸው። ብዙዎቹም በኢየሱስ አምነው ተጠመቁ።

- አንድ ሌሊት አንድ ራዕይን ተመለከተ። ጌታም በዚህ ራዕይ በቆሮንቶስ እንዲቆይና ስብከቱን እንዲቀጥል ተናገረው። በዚህም ለጌታ ብዙ ነፍሳትን ማሸነፍ ይችላል። በቆሮንቶስ ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ቆየ።

- ቆሮንቶስ እጅግ በጣም መጥፎ ከተማ ስትሆን በውስጧ የነበሩ ነዋሪዎቿ ደግሞ  እጅግ በጣም ክፉዎች ነበሩ። ጌታ ኢየሱስን ለመቀበል የወሰኑ የቆሮንቶስ ነዋሪዎች ግን ሕይወታቸው ተለውጦ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች ሆኑ።

*ይህ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ ያደረገውን ጉብኝት ታሪክ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 18፡ 1 – 17 ውስጥ ማንበብ ይቻላል።*

Copyright picture courtesy of gospelservices.com

http://gardenofpraise.com